https://www.path-2-happiness.com/am

الطريق إلى السعادة
The Path to Happiness

https://www.path-2-happiness.com/am

# መንገዱ የት አለ?!

## ማውጫ

መንገዱ የት አለ?!

ሁሉም ሰው ደስተኝነትን ይፈልጋል፤መንገዱ የት አለ?!

የአለማመን ወይስ የሃይማኖት መንገድ?!

ጥያቄዎቹ አሁንም ምላሽ ይሻሉ!!\

ታዲያ መልሶቹ እንዴት ነው የሚሆኑት?!

ማስረጃዎቹ ምንድናቸው?!

የአላህን (ሱ.ወ) አምላክነት የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች

https://www.path-2-happiness.com/am

# መንገዱ የት አለ?!

## ሁሉም ሰው ደስተኝነትን ይፈልጋል፤መንገዱ የት አለ?!

https://www.path-2-happiness.com/am

በዚህ ዓለም ላይ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው ደስተኝነትን ለማግኘት ይጥራል። ሰዎች በአመለካከታቸው፣በዘር ግንዳቸው፣በዝንባሌ እና በመርሆዎቻቸው፣በዓላማቸውና በግባቸው የሚለያዩ ቢሆኑም በአንድ ዓለማ ላይ ግን ይስማማሉ፤እሱም ሁሉም ደስተኝነትንና እርጋታን ፈላጊ መሆናቸው ነው።

ይህን ለምን ታደርጋለህ? ያንን ለምን ትሠራለህ? ብለን ማንኛውንም ሰው ብንጠይቅ፣በቃላትም ይሁን በይዘቱ በቀጥተኛ አነጋገርም ይሁን በተዘዋዋሪ ትርጉሙ ደስተኝነትን ስለምፈልግ ነው ማለቱ አይቀርም።

ደስተኝነት ምንድነው፣እንዴት ነው የምናገኘው?

ደስተኝነት ቀጣይነት ያለው የእርካታ፣የመረጋጋት፣የመታደል፣የሐሴትና የምቾት ስሜት ነው። ይህ አስደሳች ስሜት የሚመጣው ሦስት ነገሮችን በቋሚነት በመገንዘብ ነው፤እነሱም፦ የራስን ጥሩነት፣የሕይወትን በጎነትና የመጨረሻ ግብን ጥሩነት መገንዘብ ናቸው።



### ደስተኝነት ዋጋ አለው

‹‹ደስተኝነትን የማያመጣልህ ነገር ልትሰራ ትችላለህ፤የሆነ ነገር ሳታደርግ ግን ደስተኝነት አይኖርም።››

**ቤንጃሚን ዲዘራይሊ**

**የቀድሞ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር**

### ደስተኝነት ከምንም በላይ ቅርባችን ነው

‹‹ዓይናችን ላይ እያለ ብዙ ጊዜ መነጽርን እንደምንፈልግ ሁሉ፣ለእኛ ቅርብ ሆኖ እያለ ደስተኝነትን ፍለጋ እንለፋለን።››

**ቶሊስቶይ**

**ሩሲያዊ የስነጽሑፍ ሰው**

በነዚህ ሦስት ጉዳዮች ዙሪያ ነው የሰው ልጅ ለገዛ ራሱ የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች የሚጀምሩትና አብረውት እያደጉ የሚመጡት። ሰው በአእምሮው ውስጥ ለሚመላለሱ ጎትጓች ጥያቄዎች ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ ደስተኝነትን አያገኝም። ከጥያቄዎቹ መካከልም፦

- የዚህ ዩኒቨርስ ባለቤትና አስተዳዳሪው ማነው?
- እኔንና በዙሪያዬ ያለውን ፍጥረት የፈጠረው ማነው?
- እኔ ማነኝ? ከየት መጣሁ? ለምንስ ዓላማ ተፈጠርኩ? መጨረሻዬና መመለሻዬስ ወዴት ነው?

የሚሉት ይገኛሉ። የሰው ልጅ ስለራሱና ስለ ሕይወቱ ያለው ንቃተ ሕሊና እና ግንዛቤ በጨመረ ቁጥር፣የነዚህ ጥያቄዎች ጉትጎታና ጫና በአእምሮው፣በአስተሳሰቡና በመንፈሱ ላይ እየጨመረ ይሄዳል። ነፍሱ ለጥያቄዎቹ አርኪ የሆነ አሳማኝ ምላሽ እስካላገኘች ድረስ እርጋታና ደስተኝነትን አያገኝም።

### መንገዶች ቢበዙም አላህ አንድ ነው

‹‹ወዴት እየሄድክ እንደሆነ የማታውቅ ከሆነ ሁሉም መንገዶች ወደዚያ ይወስዱሃል።››



**ሉዊስ ካሮል**

**የፊዚክስ ሊቅ**

## የአለማመን ወይስ የሃይማኖት መንገድ?!

ሰዎች ከላይ ለተጠቀሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በመጀመሪያ በሁለት መንገዶች ያስባሉ። አምላክ የለም፣ዩኒቨርስ ቁስ አካል ብቻ ነው በሚለው የኤቲዝም መንገድና አላህ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ጌታ ነው ብሎ በሚያምነው መንገድ ያስባሉ። ከዚህ በመንደርደር በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ፦

- ይህ ዩኒቨርስ ተለይቶ የተወሰነለት ጊዜ ሳይኖረው በአጋጣሚ በተከሰቱ መስተጋብሮች እንዳው ራሱን በራሱ ሊያስገኝ ይችላልን?!
- ይህ ዓይነቱ የዕውር ድንብር አጋጣሚ በተራቀቀ ሥርዓት የተቀነባበረውን ዓለም ፈጠረ ብሎ ማሰብ ቻላልን?!!
- የሰው ልጅ በዘመናት ታሪኩ ውስጥ የደረሰበት ደረጃ በአዝጋሚ ለውጥ ወይም በአጋጣሚ የተገኘ ነውን?! እኛም በአጋጣሚና በሥርዓተ አልበኝነት የሚያነዳ ነፋስ የሚያሽከረክራት ቅንጣት ጥጥ እንጅ ምንም አይደለንም ማለት ነውን?
- የሰው ልጅ፣ሕግ አውጭ አምላክ፣ጥበበኛ ፈጣሪና ሁሉም ነገር እርሱ ብቻ



## አቅጣጫህን ለይ

‹‹ወዴት እንደሚሄድ ለሚያውቅ ሰው ዓለም መንገዱን ታስፋለታለች፡፡››

ራልፍ አምርሶን
አሜሪካዊ ፈላስፋ

ከርሱ ወዲያ ምንም ነውን?!

- ከስሜታዊ ግንዛቤ በላይ የሆነው ሜታፊዚካዊው ዓለም ከሞገደኛው ኢ-አማኝነትና ከተጨባጩ ዓለም ፊት መጥፋት ያለበት ሕልውና የሌለው ሲራብዱ እንጂ ሌላ ምንም አይደለም ማለት ነውን?!
- የሰው ልጅ ከማንኛውም ነገር ነጻ የሆነ ቁስ አካል ብቻ ወይም ሥር መሠረቱ በጊዜ ሂደት አዝጋሚ ለውጥ የተፈጠረ ዝንጀሮ ነውን?!
- እንዲህ ያሉ የመጠቁ ባሕርያት፣የተራቀቁ ስነ ምግባራትና አስደናቂ አወቃቀር ያሉትን ክቡሩን የሰውን ልጅ፣ግዑዝ ቁስ አካል እንዴት ሊፈጥረው ይችላል? ለራሱ የሌለውን ለሌላ እንዴት ሊሰጥ ይችላል?
- ይህች ዓለማዊ ሕይወት የሰው ልጅ የመጨረሻ ግብና የምኞቶቹ ዱካ ነች፤ስለዚህም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ከሰው በላይ ሌላ ኃይልል ስለመኖሩና ከዚህ ሕይወት ውጭ ሌላ ሕይወት ስለመኖሩ የተናገሩት ሁሉ ግምት የሚሰጠው አይደለም ማለት ነውን?

አላህ (ሱ.ወ) እንደዚያ ለሚያስቡት እንዲህ ብሏል፦

{وَقَالُواْ مَا هِيَ إِلَّا حَيَاتُنَا ٱلدُّنۡيَا نَمُوتُ وَنَحۡيَا وَمَا يُهۡلِكُنَآ إِلَّا ٱلدَّهۡرُۚ وَمَا لَهُم بِذَٰلِكَ مِنۡ عِلۡمٍۖ إِنۡ هُمۡ إِلَّا يَظُنُّونَ ٢٤} [الجاثية: ٢٤]

‹‹እርሷም (ሕይወት) የቅርቢቱ ሕይወታችን እንጅ ሌላ አይደለችም፤እንሞታለን፤ሕያውም እንኾናለን (ከፊላችን ሲሞት ከፊላችን ሕያው ይኾናል፣ይተካል) ከጊዜም (ማለፍ) በስተቀር ሌላ አያጠፋንም አሉ፤ለነርሱም በዚህ (በሚሉት) ምንም ዕውቀት የላቸውም፤እነርሱም የሚጠራጠሩ እንጅ ሌላ አይደሉም፡፡››[አልጃሢያ፡24]

የካዱ ሰዎችን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፦



አይንስታይን
የፊዚክስ ሊቅ

## ሳይንስና ሃይማኖት

‹‹ሳይንስ ከሃይማኖት ጋር የግድ ተፈጥሯዊ በሆነ የቅራኔ ሁኔታ ውስጥ መሆን አለበት ብዬ አላምንም፡፡ እውነቱን ለመናገር በሁለቱ መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩን ነው ያስተዋልኩት፡፡ ስለዚህም ሳይንስ ያለ ሃይማኖት አንካሳ ነው፤ሃይማኖትም ያለ ሳይንስ ዓይነስውር ነው፡፡ ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው፣እጅ ለእጅ ተያይዘው ይሠራሉ፡፡ የሳይንስና የሃይማኖት እውነታ ያላስደምመው ሰው በድን ሰው ሆኖ ነው የሚታየኝ፡፡››

ኒውተን
እንግሊዛዊ ፈላስፋ

## ኤቲዝም . . አንድ ዓይነት ጅልነት ነው

‹‹ኤቲዝም አንድ ዓይነት ጅልነት ነው፤የፀሐያዊ ጭፍራ ሥርዓትን ስመለከት፣ መሬት ከጸሐይ አስፈላጊውን የሙቀትና የብርሃን መጠን ማግኘት በሚያስችላት ተገቢው ርቀት ላይ መሆኗን እመለከታለሁ፤ ይህ በእርግጥ በአጋጣሚ የተከሰተ አይደለም፡፡››

{وَجَحَدُواْ بِهَا وَٱسۡتَيۡقَنَتۡهَآ أَنفُسُهُمۡ ظُلۡمًا وَعُلُوًّاۚ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ١٤} [النمل: ١٤]

‹‹እርሷም (ሕይወት) የቅርቢቱ ሕይወታችን እንጅ ሌላ አይደለችም፤እንሞታለን፤ሕያውም እንኾናለን (ከፊላችን ሲሞት ከፊላችን ሕያው ይኾናል፣ይተካል) ከጊዜም (ማለፍ) በስተቀር ሌላ አያጠፋንም አሉ፤ለነርሱም በዚህ (በሚሉት) ምንም ዕውቀት የላቸውም፤እነርሱም የሚጠራጠሩ እንጅ ሌላ አይደሉም፡፡››[አልጃሢያ፡24]

የካዱ ሰዎችን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፦

{وَجَحَدُواْ بِهَا وَٱسۡتَيۡقَنَتۡهَآ أَنفُسُهُمۡ ظُلۡمًا وَعُلُوًّاۚ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ١٤} [النمل: ١٤]

‹‹ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲኾኑ ለበደልና ለኩራት በርሷ ካዱ፤የአመጸኞችም ፍጻሜ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከት፡፡››[አልነምል፡14]

ኤቲስቶች ትንሽም ይሁን ትልቅ የማንኛውንም ፍጡር የሕይወት ምስጢር ምንነት ፈጽሞ ማወቅ አለመቻላቸውን አምነው ይቀበላሉ፡፡ ሕይወት ያለውን ነገር አንዴ ከሞተ በኋላ መልሶ ሕያው ማድረግ እንደማይችሉም እንደዚሁ አምነው ይቀበላሉ፡፡ ታድያ ይህን ዩኒቨርስ ያስገኘ ነው ብለው ብዙ የሚያወሩለት ቁስ አካል የት ገባ?! አካል በድን ቁስ አካል ከሆነ በኋላ ሕይወትን መልሶ እንዲዘራበት ቁስ አካልን ለምን አይማጸኑትም?

ኤቲስቶች እንደሚሉት ሃይማኖት ባዶ ቅዠት ቢሆን ኖሮ የሰው ልጆች እስከዚህ ደረጃ ሃይማኖትን በማክበር ላይ እንዴት ሊስማሙ ቻሉ? ነብዮች ለዘመናት ለምንድነው ስኬታማ የሆኑትና ያወረሱት ትምህርት በሰዎች ልብ ውስጥ ሕያው ሆኖ የቀጠለው፡፡ በአንጻሩ ግን የሌሎች ሰዎች አስተሳሰቦች ለዘመናት መሞትና መረሳት ብቻ ሳይሆን ባለቤቶቹ የተዋጣላቸው ተናጋሪዎች ከመሆናቸውም ጋር አሰልቺ የሚሆኑት ለምንድነው?! በጎ የሚሠራውን ክፉ

## ውበትና ሥርዓት

አፍላጦን
ግሪካዊ ፈላስፋ

‹‹ዓለም እጹብ ድንቅ ውበትና ሥርዓት አለው፤ይህ በጎውን አስቦ ሁሉንም ነገር በእቅድና በጥበብ ያቀነባበረ ሠሪ ሥራ እንጂ የአጋጣሚዎች ውጤት ሊሆን አይችልም፡፡››



https://www.path-2-happiness.com/am

## እውነተኛው ደስተኝነት

‹‹እኔ አሁን በተጨባጭ ሕይወት ውስጥ እየኖርኩ ነው። የምኖረው ግን በዛሬው ዘመናችን ሕይወት ውስጥ በምንኖርበት በዚያ አሳሳች ሰብእና አይደለም።ደስተኝነትን ይሰጡናል ብሎ በማሰብ በዚያ ቁሳዊ ፍጆታዊ፣የወሲብና የአደንዛዥ እጽ ሕይወት ውስጥ አይደለም። አሁንማ በደስተኝነት የተሞላ፣በፍቅር፣በተስፋ እና በሰላም የለጸገ ዓለም አይቻለሁ።››

**ሎራን ቡስ**
**እንግሊዛዊት የሕግ ባለሞያ**

ከሚሠራው መለየት እንዴት ነው የሚቻለው? ወንጀለኛን ከወንጀል ድርጊቱ እንዲታቀብ የሚያደርገውስ ማነው? የሀብታሙን ልብ ለደሃው እንዲራራ የሚያደርገውስ ማነው? ሌባን አጭበርባሪን፣እምነት አጉዳይን፣የአደንዛዥ እጽ ተጠቃሚን . . እነዚህን ሁሉ ፍላጎታቸውን እውን እንዳያደርጉ የሚከለክላቸው ማነው?

ኤቲዝም የተንሰራፋባቸው ህብረተሰቦች በእርስ በርስ በደል፣በራስ ወዳድነት፣በሥጋዊ ፍላጎት ተገዥነትና በሌሎቹም እኩይ ተግባራት የተኩላዎች መንጋ በሚኖርበት ሁኔታ ይኖራሉ። በመሆኑም ኤቲዝም ለአስከፊ ሁኔታ፣ለአለመታደል፣ለድህነት፣እየጨመረ ለሚሄደው ጭንቀትና አለመረጋጋት ከዋነኞቹ ምክንያቶች አንዱ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَـنۡ أَعۡرَضَ عَن ذِكۡـرِي فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَـةٗ ضَنكٗا وَنَحۡشُرُهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ أَعۡمَىٰ ١٢٤} [طه: 124]

‹‹ከግሣጼም የዞረ ሰው፣ለርሱ ጠባብ ኑሮ አልለው፤በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን።››[ጣሃ፡124]

ኤቲዝም አእምሮ፣ሎጂክም ሆነ የሰው ልጅ ተፈጥሮ የማይቀበለው ብልሹ አስተሳሰብ ነው። ሳይንስን የሚጻረር በመሆኑም ብዙ ሳይንቲስቶች ውድቅ ያደርጉታል። ይህን በእጹብ ድንቅ ሥራ የተፈጠረውን ዩኒቨርስ ባልታወቀ አጋጣሚ ተገኘ ብሎ ስለሚያምን ሕይወት ውስጥ ሎጂክ የለም በሚል መነሻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከስነ አስተሳሰብ ጋር ይጻረራል። ጤናማ ተፈጥሮ ኢአማኝ ነን በሚሉት ዘንድ እንኳ ለሃይማኖት ጥሪ የሚያደርግ በመሆኑ ኤቲዝም ከትክክለኛ ሰብአዊ ተፈጥሮ ጋርም ይጋጫል።

{وَجَحَدُواْ بِهَا وَٱسۡتَيۡقَنَتۡهَآ أَنفُسُهُمۡ ظُلۡمٗا وَعُلُوّٗاۚ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ١٤} [النمل: ١٤]

‹‹ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲኾኑ ለበደልና ለኩራት በርሷ ካዱ፤የአመጸኞችም ፍጻሜ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከት።››[አል ነምል፡14]

## ጥያቄዎቹ አሁንም ምላሽ ይሻሉ!!

የሰው ልጅ የነዚህን ጥያቄዎች ምላሽ በገዛ ራሱ ብቻ ለማወቅ የሚያደርገው ጥረት ከንቱ ነው። መሰል ጉዳዮች በሃይማኖት ክልል ውስጥ የሚገቡ በመሆናቸው፣ዘመናዊው ሳይንስ ከነዚህ ጥያቄዎች ለአንዱ እንኳ ምላሽ መስጠት አልቻለም። በዚህም ምክንያት በጥያቄዎቹ ዙሪያ የተለያዩ ዘገባዎች፣በርካታ ውዥንብሮችና አፈ ተረቶች፣በሰው ላይ ግርታና ጭንቀትን በሚያባብስ ሁኔታ ሲናፈሱ ይስተዋላሉ። በመሆኑም የሰው ልጅ አላህ ወደ ደህንነትና እርጋታ፣ወደ መታደልና ደስተኝነት መዳረሻ ወደሚያደርሰው ትክክለኛው መንገድ ካልመራው በስተቀር፣ለነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢና በቂ መልስ ማግኘት አይቻለውም።

እነዚህ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ከሰው ልጅ ሕዋሳዊ ግንዛቤ በላይ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ የሚቆጠሩ በመሆናቸው በነዚህና በመሰል ጉዳዮች ላይ መወሰን የሚችሉት ሃይማኖቶች ብቻ ናቸው። በብቸኝነት እውነታውን መንገርና ሐቁን ማሳወቅ የሚችለውም፣አላህ ወደ ነብዮቹና ወደ መልክተኞቹ ያስተላለፈው እውነተኛው ሃይማኖት ብቻ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ إِنَّ هُدَى ٱللَّهِ هُوَ ٱلۡهُدَىٰۗ} [البقرة: ١٢٠]

‹‹የአላህ መመራት (ትክክለኛው) መመራት እርሱ ብቻ ነው በላቸው፤›› [አል በቀራህ፡120]



## ደስተኝነትን ዓላማ አድርግ

‹‹ደስተኛ ለመሆን ከፈለግህ ደስተኝነትን ከግለሰብ ወይም ከሌላ ነገር ጋር ሳይሆን ከዓለማ ጋር አስተሳስረው።››

**አንሽታይን**
**የፊዚክስ ሊቅ**

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

## ታዲያ መልሶቹ እንዴት ነው የሚሆኑት?!

‹‹መምሪያው የአላህ መምሪያ ብቻ ነው በላቸው፤›› [አል ዒምራን:73]

ስለዚህም እውነተኛውን ሃይማኖት መፈለግ፣መማርና በርሱ ማመን የሰው ልጅ ግዴታ ይሆናል። በዚህም ነው ግራ መጋባትና ጥርጣሬዎች ተወግደውለት፣ወደ ቀጥተኛው የአላህ መንገድና ወደ መታደልና መረጋጋት መንገድ የሚመራው።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ مِن سُلَٰلَةٖ مِّن طِينٖ ﴿١٢﴾ ثُمَّ جَعَلۡنَٰهُ نُطۡفَةٗ فِي قَرَارٖ مَّكِينٖ ﴿١٣﴾ ثُمَّ خَلَقۡنَا ٱلنُّطۡفَةَ عَلَقَةٗ فَخَلَقۡنَا ٱلۡعَلَقَةَ مُضۡغَةٗ فَخَلَقۡنَا ٱلۡمُضۡغَةَ عِظَٰمٗا فَكَسَوۡنَا ٱلۡعِظَٰمَ لَحۡمٗا ثُمَّ أَنشَأۡنَٰهُ خَلۡقًا ءَاخَرَۚ فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ أَحۡسَنُ ٱلۡخَٰلِقِينَ ﴿١٤﴾ ثُمَّ إِنَّكُم بَعۡدَ ذَٰلِكَ لَمَيِّتُونَ ﴿١٥﴾ ثُمَّ إِنَّكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ تُبۡعَثُونَ ﴿١٦﴾}[المؤمنون: ١٢-١٦]

‹‹በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው። ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍቶት ጠብታ አደረግነው። ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፤የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን፤ቁራጭዋንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፤አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው፤ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው፤ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የኾነው አላህ ላቀ። ከዚያም እናንተ ከዚህ በኋላ በእርግጥ ሟቾች ናችሁ። ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን ትቀሰቀሳላችሁ።››[አል ሙእምኑን:12-16]

እናም የመጨረሻው መጣፊያ መንቃትና ወደ አላህ መመለስ ብቻ ነው። አላህ በከንቱ ከመፍጠር የላቀ ነውና ይህ ፍጥረት ለታላቅ ጥበብና ምስጢር እንጅ ከቶም ለከንቱ አልነበረም። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَحَسِبۡتُمۡ أَنَّمَا خَلَقۡنَٰكُمۡ عَبَثٗا وَأَنَّكُمۡ إِلَيۡنَا لَا تُرۡجَعُونَ ﴿١١٥﴾} [المؤمنون: ٢٤]

‹‹የፈጠርናችሁ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን? (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን?)።›› [አል ሙእምኑን:24]

እናም አላህ ጋኔንና ሰውን እርሱን ብቻ ያለ ምንም ማጋራት እንዲያመልኩትና እንዲገዙት እንጂ ለከንቱ አልፈጠራቸውም። አምልኮውም በተሟላ ትርጉሙና ጽንሰ ሀሳቡ፣ግዴታዎችን፣ሶላትና ውዳሴን (ዝክርን)፣ምድርን ማልማት፣ለሰው ልጆች መጥቀምን የመሳሰሉና አላህ የሚወዳቸውን ነገሮች ሁሉ በመፈጸም የሚገለጽ አጠቃላይ ዘት ያለው አምልኮ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ إِنَّ ٱلۡهُدَىٰ هُدَى ٱللَّهِ} [آل عمران: ٧٣]

{وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ﴿٥٦﴾} [الذاريات: ٥٦]

‹‹ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።›› [አል ዛርያት:56]

መላው የሰው ልጅና ፍጥረታት በሙሉ ወደርሱ ተመላሾችና መጨረሻቸውም ወደርሱ ብቻ ነው ።አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِلَى ٱللَّهِ ٱلۡمَصِيرُ ﴿٢٨﴾} [آل عمران: ٢٨]

‹‹መመለሻም ወደ አላህ ብቻ ነው።››[ኣል ዒምራን:28]

ይህ የተረጋገጠ እውነታ ከሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከንቱነትን ያስወገዳል፤ለሕይወታቸው ትርጉም በመስጠትም የሕሊና ደስታና መረጋጋትን ያጎናጽፋቸዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَمْ خُلِقُوا۟ مِنْ غَيْرِ شَىْءٍ أَمْ هُمُ ٱلْخَـٰلِقُونَ ﴿٣٥﴾ أَمْ خَلَقُوا۟ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ ۚ بَل لَّا يُوقِنُونَ ﴿٣٦﴾}[الطور: ٣٥-٣٦]

‹‹ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸው? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም አያረጋግጡም።››[አል ጡር፡35-36]

ዴካርት
ፈረንሳዊ ፈላስፋ

የሰው ልጅ የዚህን ዩኒቨርስ ምስጢር ማወቅ ተስኖት ደካማ ሆኖ በሚቆምበት ጊዜ፤በአላህ ፍጥረታት፣በምድሩ፣በከዋክብቱና በተቀሩት ጠፈራዊ አካላት፣በቀንና ሌሊት መተካካት፣በሕይወትና በሞት . . በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ አላህ ስለ አስገኛቸው ፍጥረታት በጥቅሉ አስተውሎ ያስተነትናል። ይህን ካደረገ ከርሱ ይበልጥ ኃያል የሆነ፣ሊገዛውና ሊታዘዘው የሚገባ፣ምንዳውን የሚከጅልና ቅጣቱን የሚፈራ ኃያል የሆነ ፈጣሪ አምላክ መኖሩን በተፈጥሮው አውቆ ያረጋግጣል። በዚህ ሁኔታ ዩኒቨርስን ማስተንተን ኃያል ቻይና ጥበበኛ የሆነ ፈጣሪ ስለመኖሩ፣ቁስ አካል ካለመኖር በኋላ ወደ መኖር የመጣ ከፍጥረታቱ ውስጥ አንዱ ፍጡር እንጅ ሌላ አለመሆኑን አምኖ ይቀበላል።

ይህን ራሱን ለፍጡራን አገልጋዮቹ ያስተዋወቀው፣ጥራት ይገባውና ከዚህ የተብቃቃ እየሆነ አንቀጾቹንና ምልክቶቹን ምስክርና ማስረጃ አድርጎ የሰጣቸውን፣ራሱን በምሉእ ባህርያት የገለጸውን ጥበበኛ ቻይ አምላክ፣ሕልውናውን፣ጌታነቱንና አምላክነቱን መለኮታዊ ሃይማኖቶች፣አስገዳጅ አእምሯዊ እሳቤና ጤናማ ተፈጥሮ ያረጋገጡ ሲሆን ሕዝቦች ሁሉ በሙሉ ድምጽ ይስማሙበታል።

## የሁሉም ነገር ፈጣሪ

‹‹እኔ ሕልውና አለኝ፣አለሁ። ማነው ያስገኘኝ? ማነው የፈጠረኝ? ራሴን በራሴ አልፈጠርኩም፤እናም የግድ የፈጠረኝ መኖር አለበት። ይህ ፈጣሪም የግዴታ ሕልውና ያለውና መኖር ያለበት፣አስገኝ የማያስፈልገው ወይም ሕልውናውን የሚጠብቅለት የማያሻው ሲሆን በሁሉም የውበት ባህርያት የሚገለጽ መሆንም የግድ ነው። ይህ ፈጣሪ ሁሉንም ነገር የፈጠረው አላህ ነው።››

## አጥጋቢ ምላሽ

‹‹የሃይማኖት ታሪክ በአጠቃላይ የተውሒድ ታሪክ ደግሞ በተለይ፣በአንድ አላህ ማመን ስለ ዩኒቨርስና ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠርና የተፈጠሩበትን ዓላማ አስመልክቶ ለሚነሳ ጥያቄ ብቸኛው አጥጋቢ ምላሽ ነው። ለሰብአዊ ፍጡራን ሕይወት ከአንድ አላህ በስተቀር ሌላ ግብ ሊኖር አይችልም። በሰው ልጅ ዘንድ ያለው ሃይማኖተኝነት መነሻ መሰረቱ - ተገንዝቦትም ሆነ ሳይገነዘብ - በአንድ አምላክ ያለው እምነት ነው።››

ካርዲናል ኮይንግ
የኦስትሪያ ሊቀ ጳጳስ

https://www.path-2-happiness.com/am

## ማስረጃዎቹ ምንድናቸው?!

### 1- የሚስተዋለው የአላህ ዩኒቨርስና በውስጡ ያለው ድንቅ ፈጠራ

- ይህን ግዙፍ ዩኒቨርስና በውስጡ ያቀፋቸውን ሰማያት ምድሮችና ጠፈራዊ አካላት አታዩምን?!
- ስለ ሰማያት አፈጣጠር፣ስለ ከዋክብትና ስለ ጋላክሲዎች አስበውና አስተንትነው ያውቃሉ?!
- ስለዚች ምድራችንና ስላቀፈቻቸው ወንዞች፣ባሕሮች፣ተራሮችና ሸለቆዎችስ አስበው አስተንትነው ያውቃሉ?!
- የሚስተዋልባቸው እጹብ ድንቅ አፈጣጠር፣ቅንብርና ቅንጅት አያስደምምዎትም?!



ለመሆኑ ይህን ድንቅ ዩኒቨርስ ያስገኘው፣የፈጠረውና በዚህ ተኣምራዊ አኳኋን ያሳመረው፣ያለ ምንም የቀደመ አምሳያ በዚህ ታላቅ ምሉእነት ከምንም ጀምሮ የሠራው ማነው?! ራሱን በራሱ ፈጠረ ብለው ይገምታሉ?! ወይስ ይህ ዩኒቨርስ ኃያል ችሎታ ያለው ፈጣሪ ጌታ አለው ብለው ያስባሉ?

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ لَأٓيَٰتٖ لِّأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ۝١٩٠ ٱلَّذِينَ يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمٗا وَقُعُودٗا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمۡ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ رَبَّنَا مَا خَلَقۡتَ هَٰذَا بَٰطِلٗا سُبۡحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ۝١٩١} [آل عمران: ١٩٠-١٩١]

‹‹ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር፣ሌሊትና ቀንም በመተካካት፣ለባለ አእምሮዎች ምልክቶች አሉ። (እነርሱም) እነዚያ ቆመው ተቀምጠውም፣በጎኖቻቸው ተጋድመውም፣አላህን የሚያወሱ፣በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ ፦ ጌታችን ሆይ! ይኸን በከንቱ አልፈጠርከውም፣ጥራት ይገባህ፣ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን የሚሉ ናቸው።››[አል ዒምራን:190-191]

ስለ ራስዎት አፈጣጠርና ምንነት በአእምሮ አሰላስለው አያውቁም? አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦



**አላህ እውነት ነው**

‹‹በጥልቀት ከተመራመርክ ሳይንስ በአላህ መኖር እንድታምን ያስገድደሃል።››

**ሎርድ ኬልቪ**

**እስኮትላንዳዊ የፊዚክስ ሊቅ**

{وَفِيٓ أَنفُسِكُمۡۚ أَفَلَا تُبۡصِرُونَ ۝٢١} [الذاريات: ٢١]

‹‹በነፍሶቻችሁም ውስጥ (ምልክቶች አሉ)፤ታዲያ አትመለከቱምን? ።›› [አልዛሪያት:24]

የሰው ልጅ እንዴት ተፈጠረ? አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَمۡ خُلِقُواْ مِنۡ غَيۡرِ شَيۡءٍ أَمۡ هُمُ ٱلۡخَٰلِقُونَ ۝٣٥ أَمۡ خَلَقُواْ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۚ بَل لَّا يُوقِنُونَ ۝٣٦}[الطور: ٣٦-٣٥]

‹‹ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም አያረጋግጡም።›› [አል ጡር:35-36]

ከምንም ያልተፈጠሩ ከሆኑና ራሳቸውንም ያልፈጠሩ፣ሰማያትና ምድርንም ያልፈጠሩ እስከሆኑ ድረስ ይህን ዩኒቨርስና ያቀፋቸውን ፍጥረታት በመላ ያስገኘና የፈጠረ ፈጣሪ መኖሩ ጥርጥር የለውም፤እርሱም አላህ (ሱ.ወ) ነው። ከዚህ ሁሉ አመላካች ማስረጃዎች በኋላ፣መጥኔ አቅዶና ቀርጾ የፈጠራቸውን ፈጣሪ አምላክ የአላህን መኖር ለሚክዱ ወገኖች!!

**የተፈጥሮ ስሜት**

‹‹መኖሩን አምነን ምንቀበለው አምላክ ከቁሳዊው ዓለም አይደለም፤ውስን የሆነው ሕዋሳዊ ግንዛቤያችንም ሊደርስበት አይችልም። ስለዚህም የተፈጥሮ ሳይንስን በመጠቀም የርሱን ሕልውና ለማረጋገጥ መሞከር ከንቱ ነው፤እርሱ ከውስኑ [የተፈጥሮ ሳይንስ] ክልል በላይ ነውና። በአላህ መኖር ማመን በሰው ልጅ ስሜትና ልቦናው ውስጥ አቆጥቅጠው በግላዊ ተሞክሮው ክልል ውስጥ ከሚለመልሙ ግላዊ ጉዳዮች አንዱ ነው።››

**ሮበርት ሞሪስ ቢግ**

**የተፈጥሮ ሳይንስ ሊቅ**

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

## 2- ሰብአዊ ተፈጥሮ ፦

የሰው ልጆች ያለ ጥርጥር ፈጣሪ አምላክ መኖሩን አምነው የመቀበል ተፈጥሮ ይዘው ይወለዳሉ። መልካሙን መውደድና ክፉን መጥላትም የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ማስረጃ እንኳ በማያሻው ሁኔታ ፈጣሪ መኖሩን አምኖ መቀበል ከምንም በላይ በሰው ልጅ ውስጥ ሰርጾ የጸና ተፈጥሮው ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِى فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ ٱللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾} [الروم: ٣٠]

‹‹ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህ ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃማኖት ያዙዋት)፤የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም።››[አል ሩም፡30]

ነብዩም ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ማንኛውም ሕጻን በተፈጥሮ ላይ ሆኖ እንጅ አይወለድም።››

## 3- ሕዝቦች በሙሉ ድምጽ የተስማሙበት መሆኑ ፦

ሕዝቦች ከጥንት ጀምሮ የዩኒቨርሱ ፈጣሪ አምላክ አላህ በመሆኑ ላይ ስምምነት አላቸው። በመሆኑም አላህ (ሱ.ወ) ያለ ተፎካካሪና ያለ ምንም ሸሪክ የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪ ጌታ የመሆኑ እውነታ የጸና መሰረት ያለው የጋራ አቋም ሊሆን ችሏል። የትኛውም ሕዝብ ከአላህ በስተቀር ሌላ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ፣ሌላ ሲሳይ ሰጭና መጋቢ አምላክ ፈጽሞ አለ አይልም። በአላህ (ሱ.ወ) ብቸኛ ጌትነት ሌሎች ባእድ አማልክትን ቢያጋሩም፣ስለፈጣሪነቱ በሚጠየቁበት ጊዜ ግን ፈጣሪነቱን ያረጋግጡለታል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَسَخَّرَ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۖ فَأَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ ﴿٦١﴾ ٱللَّهُ يَبْسُطُ ٱلرِّزْقَ لِمَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ

### በአላህ ማመን ተፈጥሯዊ ነው

‹‹መደበኛና ተፈጥሯዊ ካልሆነውና መቀበልና ማሳለጥ ከሚሳነው የሰው ልጆች የአእምሮ ዕድገት በተቃራኒ፣በመደበኛው ተፈጥሯዊ ሁኔታ የሚያድግ የሕጻናት አእምሮ በፈጣሪ አምላክ ወደማመን እንዲያዘነብሉ ያደርጋቸዋል።››

ጃስቶን ባሬት

በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ ጥናቶች ተመራማሪ



وَيَقْدِرُ لَهُۥٓ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ ﴿٦٢﴾ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّن نَّزَّلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَحْيَا بِهِ ٱلْأَرْضَ مِنۢ بَعْدِ مَوْتِهَا لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۚ قُلِ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ ﴿٦٣﴾} [العنكبوت: ٦١-٦٣]

‹‹ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ ማን እንደኾነ ብትጠይቃቸው በእርግጥ አላህ ነው፤ይሉሃል፤ታዲያ እንዴት ይመለሳሉ።››[አል ዐንከቡት፡61-63]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ لَيَقُولُنَّ خَلَقَهُنَّ ٱلْعَزِيزُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٩﴾} [الزُّخرُف : 9]

‹‹ሰማያትንና ምድርንም ማን ፈጠራቸው? ብለህ ብትጠይቃቸው አሸናፊው ዐዋቂው (አላህ) በእርግጥ ፈጠራቸው ይላሉ።››[አልዙኽሩፍ፡9]

ኤቲዝምና የአላህን (ሱ.ወ) መኖር መካድ፣ከአርቆ አስተዋዮች ጉዞ የተንጠባጠቡና የተንሻፈፈ እይታ ያላቸው ጥቂቶች ብቻ የሚያራምዱት፣በተጨባጭ ውድቀቱና ምክነቱ የተጋለጠ ክስተት እንጂ ሌላ ምንም አይደለም።

## 4- የሰብአዊ አእምሮ ግዴታ መሆኑ ፦

የአላህን መኖርና ጌትነቱን አስመልክተው ከላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች በተጨማሪ፣በዩኒቨርስ ውስጥ የሚስተዋለው ይህ ድንቅና የጸና ቅንብር ራሱን በራሱ ያልፈጠረ



### አስተዋይ ሁን

‹‹ማስተዋል የሚችል ሰው፣ከአእምሮና ከጥበብ ነፃ የሆነ ባዶ ቁስ አካል እንዲሁ በአጋጣሚ ራሱን በራሱ አስገኘ ብሎ መገመት ወይም ማመን ይችላልን?!››

ጆን ክሊፍላንድ ኮሥራን

በጆልስ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ፕሮፌሰር

## ፍልስፍና እና ሃይማኖት

‹‹አነስተኛ ፍልስፍና ሰውን ወደ ኤቲዝም ሲያቀርብ፣ጥልቀት ያለው ሰፊ ፍልስፍና ግን ወደ ሃይማኖት ይመልሰዋል።››

ፍራንሲስ ቤኮን

እንግሊዛዊ ፈላስፋ

https://www.path-2-happiness.com/am

ስለመሆኑ ሰብአዊ አእምሮ ከዋነኛ አስረጅዎች አንዱ ነው። ራሱን በራሱ ያልፈጠረና ያላስገኘ እስከሆነ ድረስም ያልነበረና አዲስ የተገኘ ነው፤አዲስ የተገኘኘ ነገር ደግሞ ያለ አንዳች ጥርጥር ያስገኘውና የጀመረው ፈጣሪ የግድ ይኖረዋል ማለት ነው።

እዚህ የሚነሳው ጥያቄ ፦ ስንት ጭንቅ ስንት መከራና ስንት አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞን ወደ ማነው የወተወትነው? ማንን ነው የተማጸነው? ከጭንቅ እንዲገላግለን፣ከከመከራ እንዲታደገንና ከስቃይ እንዲያድነን ማንን ነው የለመነው? ወደማነው የወተወትነው? የሚለው ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذَا مَسَّ ٱلْإِنسَٰنَ ضُرٌّ دَعَا رَبَّهُۥ مُنِيبًا إِلَيْهِ ثُمَّ إِذَا خَوَّلَهُۥ نِعْمَةً مِّنْهُ نَسِىَ مَا كَانَ يَدْعُوٓا۟ إِلَيْهِ مِن قَبْلُ وَجَعَلَ لِلَّهِ أَندَادًا لِّيُضِلَّ عَن سَبِيلِهِۦ ۚ قُلْ تَمَتَّعْ بِكُفْرِكَ قَلِيلًا ۖ إِنَّكَ مِنْ أَصْحَٰبِ ٱلنَّارِ ﴿٨﴾}[الزُّمَر: ٨]

‹‹ሰውንም ጉዳት ባገኘው ጊዜ፣ጌታውን ወደርሱ ተመላሽ ኾኖ ይጠራል። ከዚያም ከርሱ ዘንድ ጸጋን በሰጠው ጊዜ ያንን ከዚያ በፊት ወደርሱ ይጸልይበት የነበረውን (መከራ) ይረሳል፤ከመንገዱ ለማሳሳትም ለአላህ ባላንጣዎችን ያደርጋል፤በክሕደት ጥቂትን ተጣቀም፤አንተ በእርግጥ ከእሳት ጓዶች ነህ በለው።››[አል ዙመር፡8]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلَّذِى يُسَيِّرُكُمْ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ ۖ حَتَّىٰٓ إِذَا كُنتُمْ فِى ٱلْفُلْكِ وَجَرَيْنَ بِهِم بِرِيحٍ طَيِّبَةٍ وَفَرِحُوا۟ بِهَا جَآءَتْهَا رِيحٌ عَاصِفٌ وَجَآءَهُمُ ٱلْمَوْجُ مِن كُلِّ مَكَانٍ وَظَنُّوٓا۟ أَنَّهُمْ أُحِيطَ بِهِمْ ۙ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ لَئِنْ أَنجَيْتَنَا مِنْ هَٰذِهِۦ لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلشَّٰكِرِينَ ﴿٢٢﴾ فَلَمَّآ أَنجَىٰهُمْ إِذَا هُمْ يَبْغُونَ فِى ٱلْأَرْضِ بِغَيْرِ ٱلْحَقِّ ۗ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّمَا بَغْيُكُمْ عَلَىٰٓ أَنفُسِكُم ۖ مَّتَٰعَ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ ثُمَّ إِلَيْنَا مَرْجِعُكُمْ فَنُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ﴿٢٣﴾}
[يونس: ٢٢-٢٣]



‹‹እርሱ (አላህ) ያ በየብስና በባሕር የሚያስኼዳችሁ ነው፤በመርከቦችም ውስጥ በኾናችሁና በነርሱም (በተሳፋሪዎቹ) በመልካም ነፋስ የተደሰቱ ኾነው (መርከቦቹ) በተንሻለሉ ጊዜ፣ኀይለኛ ነፋስ ትመጣበታለች፤ከየስፍራውም ማዕበል ይመጣባቸዋል፤እነሱም (ለጥፋት) የተከበቡ መኾናቸውን ያረጋግጣሉ፤(ያን ጊዜ) አላህን ከዚች (ጭንቅ) ብታድነን በእርግጥ ከአመስጋኞቹ እንኾናለን ሲሉ ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይለምኑታል። በአዳናቸውም ጊዜ እነሱ ወዲያውኑ ያለ አግባብ በምድር ላይ ወሰን ያልፋሉ፤እላንተ ሰዎች ሆይ! ወሰን ማለፋችሁ (ጥፋቱ) በነፍሶቻችሁ ላይ ብቻ ነው፤(እርሱም) የቅርቢቱ ሕይወት መጠቀሚያ ነው፤ከዚያም መመለሻችሁ ወደኛ ነው፣ትሠሩት የነበራችሁትንም ሁሉ እንነግራችኋለን።››[ዩኑስ፡22-23]

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذَا غَشِيَهُم مَّوْجٌ كَٱلظُّلَلِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ فَمِنْهُم مُّقْتَصِدٌ ۚ وَمَا يَجْحَدُ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَّا كُلُّ خَتَّارٍ كَفُورٍ ﴿٣٢﴾}
[لقمان: ٣٢]

‹‹እንደ ጥላዎችም የኾነ ማዕበል በሸፈናቸው ጊዜ፣አላህን ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል፤ወደ የብስም ባዳናቸው ጊዜ፣ከነሱም ትክክለኛም አልለ፤(ከነሱም የሚክድ አልለ)፤በአንቀጾቻችንም አታላይ ከዳተኛ ሁሉ እንጅ ሌላው አይክድም።››[ሉቅማን፡32]

## የአላህን (ሱ.ወ) አምላክነት የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች

ጤናማ ተፈጥሮና አመዛዛኝ አእምሮ ይህ ዩኒቨርስ ጌታ እንዳለው፣ይህ ፍጥረተ ዓለም ያስገኘው ፈጣሪ እንዳለው ካረጋገጡ፣በጌትነቱ ላይም ከተስማሙ፣ለርሱም ጌትነት ብቻ ተገዥ ከሆኑ . . በአምላክነቱ ተጋሪም ሆነ ተፎካካሪ ባላንጣ የሌለው አንድ አምላክ ብቻ መሆኑን በከፍተኛ ድምጽ ያውጃሉ። ለዚህ ጉልህ አስረጅ ከሆኑ አያሌ ምልክቶች ውስጥ የሚከተሉትን እናገኛለን፦



### ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም

‹‹የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፣የሚቤዠርም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፣ከእኔ ሌላም አምላክ የለም።›› ኢሳይ 44፡6

ብሉይ ኪዳን



ሀርሼል
እንግሊዛዊ ፈላስፋና
ስነፈለክ ተመራማሪ

## የአላህ አንድነት

‹‹የሳይንስ አድማስ በሰፋ ቁጥር ፍጹማዊ ችሎታ ያለው ፈጣሪ ጥበብ ስለመኖሩ ማስረጃዎች እየበዙና ይበልጥ እየተረጋገጡ ይመጣሉ:: የምድር ጥናት፣የስነፈለክ፣የከርሰ ምድር፣ የተፈጥሮ፣ የፊዚክስ ሊቃውንት፤ በ ጥ ረ ቶ ቻ ቸ ው ና በግኝቶቻቸው አማካይነት የፈጣሪን ቃል ከፍ ከፍ ለማድረግ የሳይንስን ቤተመቅደስ ለመመስረት የሚያስፈልገውን ሁሉ ያመቻቻሉ::››

1. ይህ ዩኒቨርስ ሁለት አምላኮች እንዴት ሆኖ ሊኖረው ይችላል?!

የሰው ልጅ አእምሮ አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን መቀበልን ግድ ይላል:: አለበለዚያ ግን - ለክርክር ያህል- ሁለት አምላኮች ቢሆኑና ተጋጭተው ልዩነት ቢፈጥሩ፣እያንዳንዱ የየራሱን ፍላጎት ማስፈጸም ቢፈልግ፣አንደኛው አንድ ነገር ሲፈልግ ሌላኛው ተቃራኒውን ቢሻ ምንድነው የሚኮነው?! አንዱ ከሌላኛው በላይ መሆኑና ሌላኛው የበታች ደካማ መሆኑ የግድ ነው:: በዚህ ሁኔታ የበታቹ ደካማ አምላክ ሊሆን ይችላልን?! ስለዚህም ሊኖር የሚችለው እውነተኛ አምላክ አንድ ብቻ ይሆናል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{مَا ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ مِن وَلَدٍ وَمَا كَانَ مَعَهُۥ مِنۡ إِلَٰهٍۚ إِذٗا لَّذَهَبَ كُلُّ إِلَٰهِۭ بِمَا خَلَقَ وَلَعَلَا بَعۡضُهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖۚ سُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يَصِفُونَ ﴿٩١﴾ عَٰلِمِ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿٩٢﴾} [المؤمنون: ٩١-٩٢]

‹‹አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፤ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም፤ያን ጊዜ፣(ሌላ አምላክ በነበረ)፣አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር፤ከፊላቸውም በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር፤አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ:: ሩቁንና ቅርቡንም ሁሉ ዐዋቂ ነው፤(በርሱ) ከሚያጋሩትም ሁሉ ከፍ አለ::››[አል ሙእሚኑን:91-92]

2. አቅምም ሆነ መላ የሌለውን፣የሰማያትና የምድር ባለቤት ያልሆነውን፣ምንም ያልፈጠረውን እና የማይፈጥረውን፣እንኳን ለሌላው ለራሱም ቢሆን ጥቅምም ሆነ ጉዳት፣ሞትም ሆነ ሕይወት ወይም ዳግም መቀስቀስን ማስገኘት የማይችል ደካማ አምላክ የሚያመልክ ሰው አስገራሚ ፍጡር ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{تَبَارَكَ ٱلَّذِى نَزَّلَ ٱلۡفُرۡقَانَ عَلَىٰ عَبۡدِهِۦ لِيَكُونَ لِلۡعَٰلَمِينَ نَذِيرًا ﴿١﴾ ٱلَّذِى لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَمۡ يَتَّخِذۡ وَلَدٗا وَلَمۡ يَكُن لَّهُۥ شَرِيكٞ فِى ٱلۡمُلۡكِ وَخَلَقَ كُلَّ شَىۡءٖ فَقَدَّرَهُۥ تَقۡدِيرٗا ﴿٢﴾ وَٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ ءَالِهَةٗ لَّا يَخۡلُقُونَ شَيۡـٔٗا وَهُمۡ يُخۡلَقُونَ وَلَا يَمۡلِكُونَ لِأَنفُسِهِمۡ ضَرّٗا وَلَا نَفۡعٗا وَلَا يَمۡلِكُونَ مَوۡتٗا وَلَا حَيَوٰةٗ وَلَا نُشُورٗا ﴿٣﴾}[الفرقان: ١-٣]

‹‹ያ ፉርቃንን (ውነትን ከውሸት ለይውን መጽሐፍ ቁርኣንን) በባሪያው ላይ፣ለዓለማት ማስፈራሪ ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብርና ጥራት ተገባው:: (እርሱ) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና የርሱ ብቻ የኾነ፣ልጅንም ያልያዘ፤በንግሥናውም ተጋሪ የሌለው፣ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና በትክክልም ያዘጋጀው ነው:: (ከሐዲዎች) ከርሱም ሌላ ምንንም የማይፈጥሩን፣እነሱም የሚፈጠሩን፣ለነፍሶቻቸውም ጉዳትን ለመከላከል፣ጥቅምንም ለማምጣት የማይችሉትን አማልክት ያዙ::››[አል ፉርቃን:1-3]

ይህ ባይሆን ኖሮና አጋሪ ሙሽሪኮች እንደሚሉት ከአላህ ጋር ወደርሱ ለማቃረብና ለማማለድ የሚመለኩ አማልክት ቢኖሩ ኖሮ፣እነዚያ አማልክት እርሱን ባመለኩና ወደርሱ መቃረቢያ መንገድን በፈለጉ ነበር:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{قُل لَّوۡ كَانَ مَعَهُۥٓ ءَالِهَةٞ كَمَا يَقُولُونَ إِذٗا لَّٱبۡتَغَوۡاْ إِلَىٰ ذِى ٱلۡعَرۡشِ سَبِيلٗا ﴿٤٢﴾ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يَقُولُونَ عُلُوّٗا كَبِيرٗا ﴿٤٣﴾} [الإسراء: ٤٢-٤٣]

‹‹(ሙሐመድ ሆይ) በላቸው፦ እንደምትሉት ከርሱ ጋር አማልክት በነበሩ ኖሮ ያን ጊዜ ወደ ዐርሹ (ወደ ዙፋኑ) ባለቤት መንገድን በፈለጉ ነበር:: ጥራት ይገባው፤ከሚሉትም ነገር ሁሉ ከፍ ያለን ልቅና ላቀ::››[አል እስራእ:42-43]

እርሱ ግን ከማንምና ከምንም የተብቃቃ የሁሉም መጠጊያ፣ያልወለደና ያልተወለደ፣ምንም አምሳያ የሌለው አንድ አላህ ነው::

እነዚያ አማልክት ግን ምንንም ማድረግ የማይችሉና ምንም ሥልጣን የሌላቸው ደካሞች ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{قُلِ ٱدۡعُواْ ٱلَّذِينَ زَعَمۡتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ لَا يَمۡلِكُونَ مِثۡقَالَ ذَرَّةٖ فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا فِى ٱلۡأَرۡضِ وَمَا لَهُمۡ فِيهِمَا مِن شِرۡكٖ وَمَا لَهُۥ مِنۡهُم مِّن ظَهِيرٖ ﴿٢٢﴾ وَلَا تَنفَعُ ٱلشَّفَٰعَةُ عِندَهُۥٓ إِلَّا لِمَنۡ أَذِنَ لَهُۥ}[سبأ: ٢٢-٢٣]

‹‹እነዚያን ከአላህ ሌላ (አማልክት ብላችሁ) የምታስሰቧቸውን ጥሩ፤በሰማትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንንም አይችሉም፤ለነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም፤ከነርሱም ለርሱ ምንም አጋዥ የለውም በላቸው:: ምልጃም፣እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢኾን እንጂ እርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም፤ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጠም ጊዜ፣(ተማላጆቹ) ጌታችሁ ምን አለ? ይላሉ፤(አማላጆቹ) እውነትን አለ፤እርሱም ከፍተኛው ታላቁ ጌታ ነው፣ይላሉ::››[ሰበእ:22-23]

መጥቀምም ሆነ መጉዳት የማይችሉትን ፍጡራን አማልክት አድርገው በአላህ የሚያጋሩትን ሙሽሪኮች፣አቅም የለሽነታቸውን በማሳመንና ፍጡራንን ማምለክ ውድቅ መሆኑን በማስረዳት፦ ጥሪያችሁ የሚጠቅም ከሆነ ከአላህ ጋር የምታጋሯቸውን አማልክቶቻችሁን ጥሯቸው፣በማንኛውም

https://www.path-2-happiness.com/am

መልኩ መልስ መስጠት የማይችሉ አቅም የለሾች መሆናቸው ተረጋግጧልና ቅንጣት ያህል ሥልጣን በሰማያትም ሆነ በምድር ላይ በግላችሁም ሆነ በተጋሪነት የላችሁም፤እነዚያ የናንተ አማልክት በሰማያትም ሆነ በምድር ይብዛም ይነስ ምንም የሚጋሩት ነገር የላቸውም፤የግላቸውም ይሁን የጋራ ንግሥና የላቸውም፣በላቸው። ይህም ሆኖ ግን ለእውነተኛው የንግሥና ባለቤት ረዳቶችና ተጠሪዎች ሊሆኑ ስለሚችሉ እነሱን ማምለክ፣ንጉሡ ስለሚፈልጋቸው ለሚያመልኩባቸው ሰዎች በአማላጅነት ጉዳይ ያስፈጽማሉ ሊባል ይችል ይሆናል፤አላህ (ሱ.ወ) ግን ይህንንም ሲያስተባብል እንዲህ ብለዋል፦ ለርሱ ለኃያሉ አንድ አላህ ከነርሱም ከነዚያ አማልክት ምንም አጋዥ ግዛቱን ለማስተዳደርና ለማቀናበር አጋዥም ሆነ ምንም ረዳት የለውም

3. በተቀናጀና በተቀነባበረ ብርቱና ተአምራዊ ወጥ ሥርዓት የሚመራውን ይህን ዩኒቨርስ መመልከቱ ብቻ፣እጅግ ዐዋቂና እጅግ ቻይ የሆነ የአንድ አምላክ ቅንብር ስለመሆኑ ከሁሉም የላቀ ማስረጃ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ ﴿١٦٣﴾ إِنَّ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱلۡفُلۡكِ ٱلَّتِي تَجۡرِي فِي ٱلۡبَحۡرِ بِمَا يَنفَعُ ٱلنَّاسَ وَمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن مَّآءٖ فَأَحۡيَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَا وَبَثَّ فِيهَا مِن كُلِّ دَآبَّةٖ وَتَصۡرِيفِ ٱلرِّيَٰحِ وَٱلسَّحَابِ ٱلۡمُسَخَّرِ بَيۡنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ﴿١٦٤﴾} [البقرة: ١٦٣-١٦٤]

## ለእሳዩ ግብ

‹‹ይህ ዓለም ለአጋጣሚ ምንም ክፍተት በሌለው በዚህ ሁኔታ ይታየናል፤ይህም ብቻ ሳይሆን የአካሉ እያንዳንዱ ክፍል ወደ አንድ ግብ ያነጣጠረ ሲሆን ያም ግብ ከራሱ በላይ ወደ ሆነ ላቀ ግብ ያነጣጠረ ነው። እንዲህ እያለም ብቸኛና አንድያ ወደሆነ የመጨረሻው ግብ ይደረሳል።››



ፕሉቶ
ግሪካዊ ፈላስፋ

‹‹አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤(እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩኅ አዛኝ ነው። ሰማትንና ምድርን በመፍጠር፣ሌሊትና ቀንንም በማተካካት በዚያችም ሰዎችን በሚጠቅም ነገር (ተጭና) በባህር ላይ በምትንሻለለው ታንኳ፣አላህም ከሰማይ ባወረደው ውሃና በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው በማድረጉ፣በርሷም ውስጥ ከተንቀሳቃሽ ሁሉ በመበተኑ፣ነፋሶችንም (በየአቅጣጫው) በማገለባበጥ በሰማይና በምድር መካከል በሚንነዳውም ደመና ለሚያውቁ ሕዝቦች እርግጠኛ ምልክቶች አልሉ።››[አል በቀራህ፡ 163-164]

እናም ይህ ወጥ ቅንብርና አንዳች መዛነፍ ሳይኖርበት፣ለሰከንድ ሳይቆም - ቢቆም የዓለም ጥፋት ማለት ነውና - ለዘመናት የቀጠለው ሥርዓተ ዩኒቨርስ፣ይህን ማድረግ የሚችለው አላህ ብቻ እንደመሆኑ፣ይህን ድንቅ ቅንብር የፈጠረና ያስገኘ አምላክ አምሳያና ተጋሪ የሌለው አንድ ብቸኛ አምላክ አይደለምን?! አስተውሎ ማየት ለሚችል ሁሉ፣ይህ ግልጽና ቁልጭ ባለ ሁኔታ ሁለት አምላኮች ፈጽሞ ሊኖሩ እንደማይችሉ አያመለክትምን?! አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{لَوۡ كَانَ فِيهِمَآ ءَالِهَةٌ إِلَّا ٱللَّهُ لَفَسَدَتَاۚ فَسُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ رَبِّ ٱلۡعَرۡشِ عَمَّا يَصِفُونَ ﴿٢٢﴾} [الأنبياء: ٢٢]

‹‹በሁለቱ (በሰማትና በምድር) ውስጥ ከአላህ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ በተበላሹ ነበር፤የዐርሹ ጌታ አላህም ከሚሉት ሁሉ ጠራ።››[አል አንቢያ፡22]

በሰማያትና በምድር ከአላህ በስተቀር ሌሎች አማልክት ቢኖሩ ኖሮ ሁለቱም ከአቀፎአቸው ፍጥረታት ጋር በተበላሹና በጠፉ ነበር። ፍጥረተ ዓለም እንደሚስተዋለው ሁሉ በተሟላ ሁኔታ ተበጅቶ የተቀነባበረ ወጥ ሥርዓት በመሆኑ እንከንም ሆነ ጉድለት የለበትም። እርስ በርሱ መቃረንንም ሆነ መፋለስን አያስተናግድም። ይህም አቀነባባሪው አንድ፣ጌታውም አንድ፣አምላኩም አንድ መሆኑን ያመለክታል። ሁለት አቀነባባሪዎች፣ሁለት አስተዳዳሪዎች፣ሁለትና ከዚያም



www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

**ጌታ አንድ ነው**

‹‹እግዚአብሔርም አምላክ እንደ ሆነ ታወቅ ዘንድ . . . ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም።›› ዘዳግም 4፡35 ‹‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ማንም የለም፤ከእኔም በቀር አምላክ የለም፤›› ኢሳይ 45፡5

**ብሉይ ኪዳን**

በሳይ ጌቶች ቢኖሩት ኖሮ ሥርዓቱ በተዛባና በተፋለሰ፣መሠረቱም በተናጋ ነበር። አንዱ አንድ ነገር ማድረግ ሲፈልግ ሌላው ተቃራኒውን ሲያደርግ እርስ በርስ ስለሚጋጩና ተጻራሪ ቅራኔ ውስጥ ስለሚገቡ የሁለቱን ፍላጎት ማጣጣምና ማስታረቅ ፍጹም አዳጋች ይሆናል። ያንደኛው ፍላጎት ብቻ ተፈጻሚ መሆን የሌላኛውን ደካማነትና አቅም የሌሽነት ሲያመለክት በሁሉም ነገር ላይ አንድ ፍላጎት ሊኖራቸው አይችልም። በመሆኑም ያለ ምንም ተቃውሞና ያለ አንዳች እምቢታ ፍላጎቱን ሁሉ የማስፈጸም ፍጹማዊ ኃይልና ችሎታ ያለው ምንም የማይሳነው ኃያሉ አምላክ አላህ ብቻ ይሆናል።

4. ከኣደም عليه السلام አንስቶ ኑሕን፣ኢብራሂምን፣ሙሳን፣ዒሳንና ሙሐመድን ﷺ አጣቃሎ ሁሉም ነብያትና መልእክተኖች ከኀጢያት መጠበቅን፣አስተዋይና አመዛዛኝ አእምሮን፣እውነተኛነትን፣ታማኝ አድራሽነትን፣ቅንነትንና ቀጥተኛነትን ከአላህ (ሱ.ወ) የተቸሩ ሲኾኑ፣በአላህ አንድነት

በተውሒድ እና ከአላህ በስተቀር ሊገዙት የሚገባ ሌላ እውነተኛ አምላክ ባለመኖሮ ላይ ሙሉ በሙሉ ተስማምተዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ٢٥}[الأنبياء: ٢٥]

‹‹ከአንተ በፊትም፣እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።›› [አል አንቢያ፡25]

ኑሕን عليه السلام አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوۡمِهِۦ فَقَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥٓ إِنِّيٓ أَخَافُ عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٍ عَظِيمٖ ٥٩}[الأعراف: ٥٩]

**ጌታ አንድ ነው**

‹‹ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ›› ማቴ 10፡4 ‹‹ለጌታ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ›› ማር 4፡8 ‹‹እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።›› ዮሐ 17፡3፣4

**አዲስ ኪዳን**



‹‹ኑሕን ወደ ወገኖቹ በእርግጥ ላክነው፤አላቸውም፦ ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ፤ለናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም፤እኔ በናንተ ላይ የከባድ ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁ።››[አል አዕራፍ፡59]

ስለ ነብዩ ዒሳም عليه السلام አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَقَالَ ٱلۡمَسِيحُ يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبَّكُمۡۖ إِنَّهُۥ مَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدۡ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ ٱلۡجَنَّةَ وَمَأۡوَىٰهُ ٱلنَّارُۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ ٧٢}[المائدة: ٧٢]

‹‹አልመሲሕም አለ፦ የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፤እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው፣አላህ በርሱ ላይ ገነትን እርም አደረገ፤መኖሪያውም እሳት ናት፤ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።››[አል ማእዳህ፡72]

ነብዩ ሙሐመድን ﷺ ለሕዝባቸው እንዲህ እንዲሉ አዟል፦

{قُلۡ إِنَّمَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ فَهَلۡ أَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٨}[سبأ: ٢٢-٢٣]

**የደስተኝነት አመላካች**

‹‹ከዚህ በፊት ደስተኝነትን አላውቅም ነበር፤ቁርኣንን ማንበብ ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ግን፦ ሰዎች በዚህ ዓለም ላይ ማስረጃው ከፊታቸው እያለ፣ብርሃኑ ከፊታቸው እያለ፣ለምን ያለ መመሪያ ይኳዛሉ?! እያልኩ እጠይቃለሁ፣እገረማለሁም።››

ካት ስቲተስ

**እንግሊዛዊ ዘፋኝ**

‹‹ያ ወደኔ የሚወረደው፣አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው፣ማለት ነው፤ታዲያ እናንተ ፍጹም ታዛዦች ናችሁን? በላቸው።››[አል አንቢያ፡108]

የአመዛዛኝ አእምሮ ባለቤት የሆኑ ሰዎችም በዛሬው ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ሕይወት መታደልን ያግኙ ዘንድ፣የነብዮቻቸውን ዱካ በመከተል የአላህን (ሱ.ወ) አንድነት ማረጋገጥ፣አላህ አንድዩ ጌታና አምላክ መሆኑን አምነው መቀበል ይገባቸዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{مَنۡ عَمِلَ صَٰلِحٗا مِّن ذَكَرٍ أَوۡ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤۡمِنٞ فَلَنُحۡيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةٗ طَيِّبَةٗۖ وَلَنَجۡزِيَنَّهُمۡ أَجۡرَهُم بِأَحۡسَنِ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٩٧}[النحل: 97]

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹ከወንድ ወይም ከሴት፣እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን::››[አል ነሕል፡97]

መልካም ሥራ ከእምነት ጋር ውጤቱ በዚህች ምድር ላይ ጥሩ ሕይወት ነው:: ጥሩ ሕይወት ግን የግድ በገንዘብና በሀብት የተደላደለ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: መልካም ሕይወት ሆኖ ሀብትና ቁሳዊ ጸጋ የሌለበት ሊሆን ይችላል:: በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከገንዘብ ውጭ ሕይወትን መልካምና በጎ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ:: ከነዚህ መካከል ራስን ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር ማስተሳሰር፣በርሱ ላይ መተማመን፣በርሱ ጥበቃና ረድኤት መጽናናትና መረጋጋት አንዱ ነው:: ሌላው ጤንነት፣በተሰጠው ጸጋ መርካት፣በረከት፣የሕሊና እርካታ፣ቤተሰባዊ ደስታና ፍቅር፣በሰሩት በጎ ተግባር መደሰትና በሕሊና እና በአነዋነዋር ላይ የሚያሳድረው በጎ ተጽእኖ ሲሆን ገንዘብ ከነዚህ አንዱ አላባ ብቻ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلْمَالُ وَٱلْبَنُونَ زِينَةُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ وَٱلْبَٰقِيَٰتُ ٱلصَّٰلِحَٰتُ خَيْرٌ عِندَ رَبِّكَ ثَوَابًا وَخَيْرٌ أَمَلًا ﴿٤٦﴾}
[الكهف: ٤٦]

‹‹ገንዘብና ወንዶች ልጆች የቅርቢቱ ሕይወት ጌጦች ናቸው፤መልካሞቹም ቀሪዎች (ሥራዎች)፣እጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው፤በተስፋም በላጭ ናቸው::››[አል ከህፍ፡46]

ልብ አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ እጅግ ታላቅ፣ብጹእ እና ቋሚ ከሆነ ነገር ጋር ሲተሳሰር፣የሕይወት ጥሩነት ሌላ ትርጉም፣ደስተኝነትም ሌላ ትርጉም ይኖራቸዋል::

የሰው ልጅ እምቢኝ ብሎ ካፈነገጠ ግን፣ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚዳክርበትን የአለመታደል እና የመረገምን ሁኔታ ለራሱ ወዶ ተቀብሏል ማለት ነው:: በቁጭት ልብን በሚያደማ ሀሳብ፣በጭንቀትና በሀዘን ባህር ሰምጦ ብኩን ለመሆን ቆርጧል ማለት ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{فَمَن يُرِدِ ٱللَّهُ أَن يَهْدِيَهُۥ يَشْرَحْ صَدْرَهُۥ لِلْإِسْلَٰمِ ۖ وَمَن يُرِدْ أَن يُضِلَّهُۥ يَجْعَلْ صَدْرَهُۥ ضَيِّقًا حَرَجًا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِى ٱلسَّمَآءِ}[الأنعام: ١٢٥]

‹‹አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለእስላም ይከፍትለታል፤ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ቸጋራ፣ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል::››[አል አንዓም፡125]

አላህ ሸሪክ የሌለው አንድ አምላክ መሆኑን አረጋግጦ የተቀበለ ሰው፣የሕሊና እረፍት፣ውስጣዊ እፎይታና መረጋጋትን ያገኛል:: አላህ ያጠመመው ሰው ግን - አላህ ይጠብቀንና - ልቡ የጠበበና የጨነቀው፣በሀዘንና በቁጭት የተወረረ፣ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት የራቀው ይሆናል:: ይህም በተውሒድ ያመነና በአላህ አሻርኮ የጠመመ ሰው ምሳሌ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) ሌላ ምሳሌ ሲሰጥ እንዲህ ብሏል፦

{ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا رَّجُلًا فِيهِ شُرَكَآءُ مُتَشَٰكِسُونَ وَرَجُلًا سَلَمًا لِّرَجُلٍ هَلْ يَسْتَوِيَانِ مَثَلًا ۚ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٢٩﴾}[الزمر: ٢٩]



‹‹አላህ በርሱ ተጨቃጫቂዎች የኾኑ ተጋሪዎች ያሉትን ባሪያና፣ለአንድ ሰው ብቻ ንጹሕ የኾነን ባሪያ (ለሚያጋራና ባንድነቱ ለሚያምን ሰው) ምሳሌ አደረገ፤በምሳሌ ይተካከላሉን?፤ምስጋና ለአላህ ይገባው:: በውነቱ አብዛኞቻቸው አያውቁም::››[አል ዙመር፡29]

የሙሽሪክ ሰው ምሳሌ፣አንዱ ሂድ ሌላው ተቀመጥ ሲለው ሦስተኛው ቁም የሚሉት ዓይነት ክፉ ዐመል የተጠናወታቸው ተጨቃጫቂ ጌቶች ያሉት ሰው ምሳሌ ሲሆን፣በዚህም የአካልም ሆነ የአእምሮ እረፍት አጥቶ እንደተረበሸ ይኖራል:: በአላህ አንድነት የሚያምን ሰው ምሳሌ ደግሞ ለአንድ ጌታ ብቻ ታማኝ ተገዥና ታዛዥ የሆነ ሰው ምሳሌ ነው:: ሁለቱ እኩል ሆናሉን?! አላህ (ሱ.ወ) አንድ ጌታ አንድ አምላክ ነው፤ከርሱ በስተቀር ሌላ እውነተኛ አምላክም ሆነ ሌላ እውነተኛ ጌታ የለም:: ሁሉም ምስጋና እና የላቀ ውዳሴ ለርሱ ይሁን:: እርሱን የማያውቁት ግን በከፍተኛ ውስጣዊ ግጭትና ቀውስ፣በሀሳብና በጭንቀት፣በግራ መጋባት፣በመደናበርና ራስን በማጥፋት አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ይኖራሉ::

## ራስን መግደልና ሃይማኖት

‹‹በዓለም ጤና ድርጅት (WHO) ኤክስፐርት የሆኑት ዶክተር ጆስ ማንዌል እና ተመራማሪ አሌሳንድራ ፍሊሽማን ራስን በመግደልና በሃይማኖት መካከል ያለውን ግንኙነት አጥንተው፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተረጋገጠ ሳይንሳዊ ምርምራቸው ቀጥሎ በሰፈረው ሰነድ ውስጥ በተካተተው ውጤቱ ላይ ደርሰዋል፦

A global perspective in the epidemiology of suicide






https://www.path-2-happiness.com/am